## የጋርዮሽ ጸጋ፡-

- ✓ በእርሱ ለማያምኑም ሆነ ለሚያምኑ የሰው ልጆች ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣቸው የማይየገባቸው በረከቶች
- ✓ አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ባደረጉባት ቀን ላይ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ነበር፣ የፍርድ አፈጻጸሙ ግን ለረጅም አመታት ቆይቷል
- ✓ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ልጆቻቸውም ኃጢአትን ባደረጉበት ቀን ከመሞት ይልቅ በሕይወት እየኖሩ ስፍር ቁጥር በሌለው የእግዚአብሔር በረከት እንዲኖሩ ያደርጋል

**ትርጉም፡-** የጋርዮሽ ጸጋ ማለት የደህንነት / የዘላለም ሕይወት ክፍል ያልሆኑ እጅግ የተትረፈረፉ የእግዚአብሔር በረከቶች /ፀጋዎች ናቸው

- ለመዳን የሚሆነው ጸጋ "የሚያድን ጸጋ" ይባላል ቲቶ 2፡11
- የሚያድን ጸጋ በቀጥታ ከክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ጋር የተያያዘ ነው
- የጋርዮሽ ጸጋ በተዘዋዋሪ ከክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ጋር የተያያዘ ነው

## የጋርዮሽ ጸጋ ምሳሌዎች

1. ከቁሳዊ ነገሮች አንጻር፡- ምድር እሾህና አሜከላ ብቻ ሳይሆን ምግብ፤ ውሃ ፤ልብስ ፤መጠለያ ትሰጣለች የጸሐይ ብርሀን ዝናም ወዘተ ማቴ 5፡44-45፤ ሐዋ 14፡16-17
   * እግዚአብሔር የጶጢፋርን ቤትና እርሻ ባርኮለታል ዘፍ 39፡5
   * የፍጥረቱን ሁሉ ፍላጎት ያሟላል መዝ 145፡15-16

2. ከህሊና ; አእምሮ አንጻር፡- ሰው ሁሉ ነገሮችን የሚያገናዝብበት ህሊና ተሰጥቶታል፤ ሌሎች ደግሞ ከዛም አልፈው ለሰው ልጆች የሚጠቅምን ነገር የሚሰሩበት ምጡቅ አእምሮ ተሰጥቶአቸዋል፤ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ እውነተኛውን አምላክ የሚያውቁበት እድል አላቸው (ሮሜ 1፡21 ፣ ሐዋ 17፡26)
   * አማኝ ባልሆኑ ሰዎች የተሰሩ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች የጋርዮሽ ጸጋ ማሳያዎች ናቸው

3. ከስነ ምግባር መመርያ አንጻር፡- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ በሚችሉት ኃይልና ጉልበት መጠን ኃጢአትን እንዳያደርጉ ወሰንነትን አድርጎባቸዋል፡፡
   - የህሊና ዳኝነት ዋናው ውሱንነትን አምጪ መሳርያው ነው (ሮሜ 2፡14-15)
   - ሕጎችን ፤ደንቦችን ፤አስተዳደራዊ ተቋማት እንዲቋቋሙ ያደርጋል
   - የጋብቻን አስፈላጊነት ፤ክቡርነት፤ የሕጻናትን ደህንነት እንዲጠብቁ ያረጋል
   - ለምሳሌ ስርቆት፤ መዋሸት
   - ዳሩ ግን በስነ ምግባራቸው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሊያገኙ አይችሉም ገላ3፡11፤ ሮሜ 3፡12

4. ከፈጠራ ስነጥበብ ሥራዎች አንጻር
   - አርት፣ ሙዚቃ፣ አትሌቲክስ፣ ምግብ ማብሰል፣ ስነ-ጽሐፍ
   - አንዳንዴ ከአማኞች በበለጠም ለማያምኑት ይሰጣል፤ ዘፍ 4፡21, 22

5. ከማሕበራዊ ሕይወት አንጻር
   - የተለያዩ ማሕበራዊ እሴቶች፣ መዋቅሮች
     ምሳሌ፡- አዳምና ሔዋን ባልና ሚስት መሆናቸው ቀጥሏል፡፡
     ቤተሰብ፡ ለሰው ሁሉ የተሰጠ ተቋም ነው
     መንግስታት፡ የሰዎችን ክፋትን ከምድር ለመከልከል፤ ሮሜ 13፡1-7
     ሌሎች ተቋማት፡ የትምህርት፣ የንግድ፣ በጎ አድራጎቶች

❖ የጋርዮሽ ጸጋ ደህንነትን አይሰጥም

- ✓ ሰዎችን ምናልባት የሚድኑበትን ቃል ለመስማት ያዘጋጃቸው ይሆናል እንጂ
- ✓ ምናልባት ኃጢአት በሙሉ መጠኑ እንዳይገለጥ ሊከለክል ይችላል፣ የሰውን የተደበቀ ክፋትና ሥር የሰደደ የኃጢአት ኑሮ ሊቀይር አይችልም
- ✓ ሥነ - ምግባራቸው በክርስቶስ ባለ እምነት አይደለም፣ ያለ እምነት የሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው፡፡ ሮሜ 14፡23
- ✓ ለእግዚአብሔር ባለ ፍቅር ሳይሆን ለራሳቸው ባላቸው ፍቅር ነው (Self Love)፣ ሉቃ 18፡4

## የጋርዮሽ ጸጋ ምክያቶች

1. የሚድኑት እስኪዋጁ ድረስ፡- ምናልባት ሰዎች ወደ መዳን ይመጡ ዘንድ (2ጴጥ 3፡9-10)
   - ኃጢአተኛም ቢሆኑ በሕይወት እንዲኖሩ ይፈቅድላቸዋል
2. የእግዚአብሔርን መልካምነትና ምህረት ለመግለጥ
   - የእግዚአብሔር መልካምነት በማዳን ሥራው ብቻ ሳይሆን ለማይገባቸው ኃጢአተኞችም በሚሰጣቸው ምድራዊ በረከት ጭምር ነው (ሉቃ 6፡35፣ መዝ 145፡ 9)
   - ጌታ ኢየሱስ ባለጠጋውን ሰው ምንም እንኳን እርሱን መከተል ባይፈልግም ነገርግን ወደደው (ማር 10፡21)
   - እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይወድዳል (ሕዝ 33፡11፣ 1ጢሞ 2፡4)
3. የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመግለጥ
   - ባለማመን የሚጸኑትም የእግዚአብሔርን ቁጣ በራሳቸው ላይ ያከማቻሉ (ሮሜ 2፡5)
   - በፍርድ ቀን የሰው ሁሉ አፍ ይዘጋ ዘንድ (ሮሜ 3፡19)
4. እግዚአብሔርን ክብር ለመግለጥ
   - ሰዎች በሚያደርጓቸው ነገሮች ሁሉ የእርሱ ክብር ይገለጥ ዘንድ ነው